# እንኳን፡ከዘመን፡ወደ፡ዘመን፡አሸጋገራችሁ፤

መስከረም፡፩፡ቀን፡፳፻፩፡ዓመተ፡ምሕረት፣







ዕንቁዕ፡ጣጣሽ፤

ዕንቁዕ፡ጣጣሽ፤

ከተከበሩት፡ንቡረ፡ዕድ፡ኤርምያስ፡ከበደ፡ወልደ፡እየሱስ፡መጽሐፍ፡ውስጥ፡*የተቀባው፡ጌታችን፡እና፡መድኃኒታችን፡እየሱስ፣የቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፣የአዳም፡እና፡ሔዋን፡ልደታትም፡መስከረም፡፩፡ቀን፡መሆኑን፡ስለ፡አበሠሩን፡እና፡ይኸን፡ድርብርብ፡ዓመት፡በዓል፡ለማክበር፡ስለ፡እሚያዘጋጀን፡ልዑል፡እግዚአብሔር፡ላቅ፡ያለ፡ምስጋናዬን፡አቀርባለሁ።ደግሞም፣የውጭ፡ዜጋ፡ደራሲዎች፡ኢትዮጵያዊው፡ጃንደረባ፡እያሉ፡ስም፡እንደ፡ሌለው፡የሚያፌዙብንን፡የንግሥት፡ሕንደኬን፡ዘመን፡በጅሮንድ፡ባኮስን፡ስም፡ስለ፡አሳወቁን፡ተድስቻለሁ።እናም፣ሊቀ፡ምሁር፡ለይኩን፡ብርሃኑም፡ስለ፡ምሉክ፡ባኮስ፡ራሱን፡የቻለ፡መጽሐፍ፡ለማሳተም፡ያቀዱት፡ተሳክቶ፡በበለጠ፡አንብበን፡እንደ፡እምንረዳ፡ተስፋ፡አደርጋለሁ።

በመቀጠልም፣ገበሬው፦ ከውፍ፡አፍላፍ፡አብላኝ።ነጋዴው፦ አብሮ፡የበላን፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡አይሸረውም።ብሎ፡ያገልግሉን፡ስንቅ፡የማካፈሉ፡ባሕላችንን፡እየ፡አስታወስኩ፡በሚቀጥለው፡ዓመት፡ኢትዮጵያ፡አገራችን፡ገብተን፡በሰላም፡እና፡ደስታ፡ከወገኖቻችን፡ጋራ፡እንድናከብር፡ጥኑ፡ምኞቴን፡እገልጻለሁ።

ባሕላዊ፡ቋንቋችንንም፡የውጭ፡አገር፡ቋንቋ፡በመቀላቀል፡አነጋገራችን፡እያበላሸነው፡ከመሆናችንም፡በላይ፣ ነጥበ፡ሥነ፡ሥርዓቱንም፡የሳተው፡አጻጻፋችን፡ይታሰብበት።ግዜ፡ለመቆጠብም፡ተብሎ፡እኛነታችንን፡አንጣ።ከኋላ፡ፀፀት፣ዛሬ፡በማኅበር፡ተደራጅቶ፡መበርታት።አንድ፡ሰው፣ደራሲ፡እና፡ቀማሪ፡ሲሆን፡ይዋከባል፡እና!!

በተረፈ፡የኃያሉ፡እግዚአብሔር፡ምሕረቱ፡እና፡ቡራኬው፡አይለየን።አሜን።

ከማክበር፡ሰላምታ፡ጋራ፣

ኢትዮጵያዊው፡ወገናችሁ፦
ስለሺ፡ነህ፡ገላነህ፣
ሞንትርያል፣ካናዳ።

የክቡር፡ንቡረ፡ዕድ፡ኀዋ፡ሰሌዳቸው፦ www.ekogs.org ነው፡እና፡ጐብኙት።

*ክርስቶስ፡የሚለው፡ቃል፡የግሪክ፡ቋንቋ፡ስለ፡ሆነ፣ትርጉም፡ቋንቋችንን፡ስለ፡ፈለግሁት፡ነው።

EthioLion.Com